


## የወላጆች መብቶች

# የቃልና የጽሁፍ ትርጉም አገልግሎቶች

ሁሉም ወላጆች የልጃቸውን ትምህርት አስመልክቶ እነሱ በሚገባቸው ቋንቋ መረጃ የማግኘት መብት አላቸው። ልጅዎ ትምህርት ቤት ሲመዘገብ፣ ከትምህርት ቤቱ ጋራ መልዕክት ሲለዋወጡ ምን ቋንቋ መጠቀም እንደሚፈልጉ፣ ትምህርት ቤቱ ይጠይቅዎታል። ይህ ደግሞ፣ ስለ ቋንቋ ፍላጎትዎ ትምህርት ቤቱ ለይቶ እንዲያውቅ ስለሚረዳው፣ ያለ ምንም ክፍያ የቃልና የጽሁፍ ትርጉም አገልግሎት ለማቅረብ እንዲችል ያደርገዋል።

## ከትምህርት ቤትዎና ከትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ምን መጠበቅ ይችላሉ

**እርስዎ፣ የልጅዎን ትምህርት በሚመለከት ረገድ በጣም አስፈላጊ ነዎት!**

ትምህርት ቤቱ ፣ የልጅዎን ትምህርት አስመልክቶ - በቋንቋዎ - ከእርስዎ ጋራ መነጋገር ይኖርበታል። ይህም አብዛኛውን ግዜ፣ ሰነዶችን በጽሁፍ መተርጎምንና በስብሰባዎችና በ ቃለ ልውውጦች ላይ የቋንቋ አስተርጓሚ ማቅረብን ያጠቃልላል።

የተወሰነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚናገሩ ከሆኑና ልጅዎ ደግሞ እንግሊዝኛ መናገር ወይም ማንበብ የሚችል ቢሆንም እንኳን፣ እነዚህን አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አለዎት።

ትምህርት ቤቱ ፣ ለልጅዎ የሚሆኑ አስፈላጊ መረጃዎችንና እድሎችን አስመልክቶ **በቋንቋዎ**፣ ከእርስዎ ጋራ መነጋገር ይኖርበታል። ይህም ስለሚከተሉት መረጃዎች ያካትታል፥

- ትምህርት ቤት ምዝገባና መግባት
- የትምህርት ውጤቶች፣ የአካዳሚ ደረጃዎችንና ከትምህርት ቤት መመረቅን
- የትምህርት ቤት መመሪያዎችና የተማሪ ዲስፕሊን
- በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት፣ አለመገኘትና ከትምህርት ቤት ለቆ መውጣት
- ለሚደረጉ ድርጊቶች ወይም ፕሮግራሞች የወላጅ ፈቃድ
- ጤና፣ ደህንነትና ድንገተኛ ሁኔታዎች
- የትምህርት ቤት መዘጋት
- ፕሮግራሞችን ወይም አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚኖሩ ዕድሎች - ከፍተኛ የትምህርት ችሎታ ያላቸውን፣ በከፍተኛ የትምህርት ድረጃ አዘልሎ መመደብ፣ እና ምደባና የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ ፕሮግራሞችን ጨምሮ
- በአካል ለታጎሉ ተማሪዎች የሚሆን ልዩ ትምህርትና አገልግሎቶች

**ከአስተማሪዎችና ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋራ ስብሰባዎችና ውይይቶች**

ከአስተማሪዎች ወይም የትምህርት ቤቱ ባልደረቦች ጋራ ሲነጋገሩ፣ አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ትምህርት ቤቱ አስተርጓሚ ማቅረብ ይኖርበታል። ይህም የወላጅ-አስተማሪ ጉባኤዎችን፣ ስለ ልዩ ትምህርት ስብሰባዎች፣ ወይም የልጅዎን ትምህርት አስመልክቶ ሌሎች ማናቸውንም ውይይቶች ያጠቃልላል።

ትምህርት ቤቱ የእርስዎን ቋንቋንና እንግሊዝኛን በደምብ የሚችሉ ብቁ አስተርጓሚዎችን ብቻ ነው መጠቀም ያለበት። በስብሰባው ወቅት በጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላቶችን ወይም ሃሳቦችን አስተርጋሚው የተረዳ መሆኑን ትምህርት ቤቱ ማረጋገጥ ይኖርበታል። ትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን ወይም ህጻናትን እንደ አስተርጓሚ መጠቀም የለበትም።

አስተርጓሚው ገለልተኛና በውይይቱ ወቅት ላይ የተነገረውን ሁሉንም ቃል ማስተላለፍ ይኖርበታል። ማንኛውም ሰው ከተናገረው ላይ መቀነስ ወይም በላዩ ላይ መጨመር የለባቸውም። አስተርጓሚዎች የነሱን ሚናና መረጃን በምስጢር መያስ እንዳለባቸው የተረዱ መሆናቸውን ትምህርት ቤቱ ማረጋገጥ ይኖርበታል። አስተርጓሚው በአካል ሊገኝ ወይም በስልክ ሊቀርብ የሚችል ሲሆን፣ የዲስትሪክቱ ሥራ ባልደረባ ወይም ከውጭ ባለኮንትራት ሊሆን ይችላል።

ትምህርት ቤቱ፣ የልጅዎን ትምህርት አስመልክቶ በሚደረጉ ማናቸውም ስብሰባዎች ወይም እትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረጉ ውይይቶች አስተርጓሚ ማቅረብ ይኖርበታል። አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ደግሞ ትምህርት ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ።

**የጽሁፍ መረጃ**
ትምህርት ቤቱ፣ አስፈላጊ የሆኑ በጽሑፍ የተዘጋጁ መረጃዎችን በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ውስጥ በብዛት ወደሚነገሩ ቋንቋዎች ማስተርጎም ይኖርበታል። በቋንቋዎ ያልሆነ መረጃ ከደረሰዎ፣ በቋንቋዎ በጽሁፍ እንዲተረጎምልዎ ወይም በቃል እንዲገለጽልዎ የሚፈልጉ መሆንዎን ለትምህርት ቤቱ ያሳውቁ።

## ስለ አሳሳቢ ጉዳዮች እና ብሶቶች ለመነጋገር

**መብቶችዎ እነዚህ ናቸው!**

በስቴትና በፌደራል የሕዝባዊ መብቶች ሕጎች መሠረት፣ መረጃን በራስዎ ቋንቋ የማግኘት መብት አለዎት። ስለ ትምህርት ቤቱ የቃል ወይም የጽሁፍ ትርጉም አገልግሎቶች አሳሳቢ ጉዳዮዎች ካሉዎት—ወይም የሚያስፈልግዎት የቃል አስተርጓሚ ወይም የጽሁፍ ትርጉም ቀርቦልዎት ካልነበረ—አያሌ አማራጮች አሉዎት።

1. **ከሚያመችዎ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ወይም ባልደረባ ጋራ ይነጋገሩ።** አብዛኛውን ግዜ ስለ አሳሳቢ ጉዳይዎችዎ ለመነጋገር ከትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ጋራ የሚያደርጉት ውይይት በጣም የሚሻለው የመጀመሪያ እርምጃ ነው። ምን እንደ ተከሰተ ያስረዱ፣ እናም ዲሬክተሩ እንዴት አድርገው ችግርዎን ሊፈቱልዎ እንደሚችሉ ይግለጹላቸው።

2. **ከትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎ ጋራ ይነጋገሩ።** ደግሞ ስለ አሳሳቢ ጉዳዮችዎ ለማካፈል የትምህርት ቤቱን ዲስትሪክት ማነጋገር ይችላሉ። በዲስትሪክቱ ቢሮ ለሚገኙት የሕዝባዊ መብቶች አስተባባሪ ወይም ሱፐርኢንቴንዳንት መደወል ይችላሉ።

3. **ለአሳሳቢ ጉዳዮችዎ መፍትሄ ለማግኘት እርዳታ ይጠይቁ።** ደግሞ ስለ መብቶችዎ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወይም ለአሳሳቢ ጉዳዮችዎ መፍትሄ ለማግኘት እርዳታ ለመጠየቅ እነዚህን ኤጀንሲዎች ማነጋገር ይችላሉ።

   Equity and Civil Rights Office
   Office of Superintendent of Public Instruction
   360-725-6162 | www.k12.wa.us/equity

   Office of the Education Ombuds
   206-729-3251 | oeo.wa.gov

4. **ለብሶትዎ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።** ለብሶትዎ ማመልከቻ ለማስገባት፣ ምን እንደ ተከሰተ በጽሁፍ ይግለጹ—በማንኛውም ቋንቋ—ከዚያም ለዲስትሪክቱ በፖስታ፣ በኢሜይል ይላኩ፣ ወይም በእጅ ማድረስ ይችላሉ። ለመዝገብዎ ግልባጭ ማስቀመጥዎንም ያረጋግጡ።

   ዲስትሪክቱ በ 30 ቀኖች ውስጥ፣ ያስገቡትን ብሶት መርምሮ በጽሁፍ መልስ ይልክልዎታል። ስለ ብሶትዎ ማሰሚያ አማራጮች ተጨማሪ መረጃ በኢንተርኔት በእዚህ ድረገጽ ላይ መመልከት ይችላሉ፥ www.k12.wa.us/Equity/Complaints.aspx።

አሳሳቢ ጉዳዮችዎን ወይም ብሶትዎን ስላካፈሉ ትምህርት ቤቱ በእርሶ ላይ ወይም በልጅዎ ላይ የአጸፋ እርምጃ ላይወስድ እንደሚችል ሊያውቁ ይገባል።